አሌክሳንድሪያ፡ ይዘጋጁ። ይከላከሉ ።

**የ COVID-19 ስርጭትን ይከላከሉ**

## ቫይረሶች አንዱን ከሌላው እንደማይለዩ ሁሉእ ኛም ልዩነት ማድረግ የለብንም

# ኮሮና ቫይረስ እና አድልዎ

### ኮሮና ቫይረስ በዘር፣ በዜግነት ወይም በብሔር ላይ የተመሰረተ አይደለም

የ 2019 ኖቭል ኮሮና ቫይረስ የተቀሰቀሰው ውሃን፣ በምትባል የቻይና ከተማ ውስጥ ነው። ይህ መልክዓ ምድርን ለመግለጽ አገላለጽ ነው። የቻይና ሀር ሃረግ መኖር ወይም የሌላ ማንኛውም ሀር ሃረግ መኖሩ አንድን ሰው ለዚህ በሽታ የበለጠ ተጋላጭ አያደርገውም።

### የፊት መሸፈኛ ማስክ መሸፈን ሰዉን ህመምተኛ አያደርግም።

ሰዎች በተለያዩ ምክንያቶች ማስክ የሚያደርጉ ሲሆን፣ ይህም የ ከአበባ ብናኝ ከአየር ከሚመነጭ ብክለት ለመከላከልና በባሕላዊና ማሕበራዊ ምክንያቶች ሊጠቀሙ ይችላሉ። አንድ ሰው ማስክ በማድረጉ መፍረድ ወይም ሕመምተኛ ነው የሚል ግምት መያዝ የለብንም።

### የተሳሳተ ትዝብትዎ ማቋረጥ ይችላሉ። ትክክለኛ መረጃን ከማጋራት ይጀምሩ።

የተሳሳተ መረጃን ከማሰራጨት ይቆጠቡ። ከሚታወቁና ተዓማኒ ከሆኑ ምንጮች መረጃዎችን ይከታተሉ፡

- Centers for Disease Control and Prevention
- Virginia Department of Health
- Alexandria Health Department

### የተሳሳተ መረጃ ሰዎችን የማስፈራራት ነገር ከሰሙ፣ ከተመለከቱ ወይም ካነበቡ ድምጽዎን ያሰሙ።

የተሳሳተውን መረጃ በአግባቡ ያርሙና ለተናጋሪው አድሎአዊ ንግግሮች እና እርምጃዎች የሁላችንንም ደህንነት ይበልጥ እንዲያሰ ያደርጉታል። ከበድ ያለ የማስፈራራት ሁኔታ ከተከሰተ፣ ሪፖርት ስለማድረግ ያስቡ። የመረጃ ምንጮችን በዚህ ያግኙ፡ **alexandriava.gov/Coronavirus**

### ይበልጥ ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች ርህራሄና ድጋፍ ያሳዩ።

በት/ቤቶችም ሆነ በስራ ቦታዎች፣ ለተማሪዎችና ሰራተኞች ዘረኛና የተዛቡ ሃሳቦችን የሚያከሽፉ የመማሪያ ዕድሎችን ይፍጠሩ። አድልዎና መገለል የሚፈጸምባቸውን የሰዎች ታሪክ ያድምጡ፣ ይገንዘቡ እንዲሁም ፈቃድ ሲሰጥዎት ታሪካቸውን ያጋሩ፣ አድሎአዊነት በማህበረሰብዎ ዉስጥ ውስጥ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑም መልእክት ያጋሩ።

**ለማንቂያ መልእክቶች፣ ALEXCOVID19 ብለው ወደ 888777 ይላኩ**

**አሌክሳንድርያ ኮቪድ-19 የኢንፎርሜሽን መስመር:** 703.746.4988 ከሰኞ-አርብ 9am-6pm

3.25.20

**ከአሌክሳንደሪያ የጤና መምሪያ በጣም የቅርብ ጊዜ መረጃዎችን ለማግኘት፣ ይህን ይጎብኙ፡**

**ALEXANDRIAVA.GOV/CORONAVIRUS**

የ King County, WA መረጃ።